## በወገኖቻችን ላይ በሳውዲ አረቢያ የሚፈፀመው ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት ከምንጩ ሊደርቅ ይገባል!

የኢትዮጵያ ወጣቶች ብሄራዊ ንቅናቄ በኢትዮጵያውያን እህትና ወንድሞቻችን ላይ በሳውዲ አረቢያ እየተፈጸሙ ባሉት እንግልቶች፣ ድብደባዎች፣ አስገድዶ መድፈሮች፣ ግድያዎችና፣ ሌሎች ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶች የተሰማውን ጥልቅ ሃዘንና ምሬት እየገለፀ፤ እነኝህን እጅግ የሚያስቆጡ፤ ህዝባችንን በጅምላ የመጨፍጨፍና ብሄራዊ ክብራችንን የማዋረድ ዘመቻዎችን አጥብቆ ያወግዛል፤ ይታገላል። በመሆኑም ንቅናቄአችን የተጫነብንን አደጋ ግንባር ቀደም ሆኖ ለመጋፈጥ የበደሉ ገፈት ቀማሽ ከሆነው ህዝባችን ጎን እስከመጨረሻው እንደሚቆም ከወዲሁ ያረጋግጣል።

ውድ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን፤ እየተፈፀሙብን የሚገኙት ለጆሮ የሚከብዱ አሳዛኝ በደሎች፣ ሰቆቃዎችና፣ ብሄራዊ ውርደቶች ያለምክንያት የመጡ አይደሉም። ይልቁንስ፤ ላለፉት 22 አመታት የምንወዳት ሃገራችን ኢትዮጵያንና የምንከበርበት የኢትዮጵያዊነት ኩራታችንን ለማጥፋት በወያኔ መራሹ የኢህአዴግ መንግስት ከተወጠኑ ትውልድን የማምከን ዘመቻ አንዱ አካል እንደሆኑ፤ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በግልጽ መገነዘብ ይችል ዘንድ የምስክርነት ማሳያዎችና፤ ትውልዳዊ ሃላፊነቶቻችንን የመወጣት ቀናይነትንና ብቃትን በተግባር ልናሳይ የሚያስገድዱን፤ ፈታኝ ታሪካዊ አጋጣሚዎች መሆናቸውን የኢትዮጵያ ወጣቶች ብሄራዊ ንቅናቄ በአፅንዖት እያሳሰበ፤ ይህንን አስከፊ በደል ለማስቆም በመላው አለም በአንድነት አጋርነቱን በማሳየት ላይ ላለውና፤ በየሃገራቱ በሚገኙ የሳውዲ አረቢያ ኢምባሲዎች ደጃፍ ላይ የተቃውሞ ድምፁን በማሰማት ላይ ለሚገኘው ኩሩና ቆራጥ ኢትዮጵያዊ ወገናችን ያለውን ወሰን የለሽ ክብርና አድናቆት ለመግለጽ ይወዳል።

ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን የሚወዷት ሃገራቸውን፣ የሚሳሱላቸው ልጆቻቸውን፣ ቤተሰቦቻቸውንና፣ ወዳጆቻቸውን ትተው የቤት ሰራተኛ ለመሆን ወደ አረብ ሃገራት ሲሰደዱ፤ በወያኔ/ኢህአዴግ የተፈጠሩብንን ውስብስብ የሞራል፣ የፖለቲካ፣ የማህበረሰባዊና፣ በዋነኝነት ደግሞ የኢኮኖሚ ጫናዎችና ፈተናዎችን ለመቋቋም፤ ኑሮን የማሸነፍ ተስፋን ሰንቀው እንጂ፤ በአረብ ሃገራት የምቾት ኑሮ ይጠብቀናል ብለው እንዳልሆነ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ልብ ያውቀዋል። እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ፤ ህይወታችን ቢቃና ብለው የጀመሩት ጉዞ ህይወት ሲያስከፍል፤ ከሰብዓዊነት በታች ሲያዋርድ፤ የወንድሞቻችንን ደረት ለጥይትና የእህቶቻችንን አንገት ለገመድ ሲዳርግ ማየት ሃዘናችንን እጅግ መሪር ያደርገዋል።

ለተቸገሩ መጠለያ፣ ለታረዙ ልብስን፣ ለተራቡ ምግብን እንካችሁ በሚለው ሩህሩህና አኩሪ ታሪኩ የሚታወቀው ክቡር ህዝባችን፤ ዛሬ ሃገርና ወገን እንደሌለው ሁሉ፤ ደምህ ደመ-ከልብ ይሁን ተብሎ ሲፈረድበት ማየት በእጅጉ ልብ ይሰብራል። ለዚህ ታሪካዊ ውድቀት ዋንኛ ተጠያቂው፤ ጥቅምና ስልጣኑን ለማስጠበቅና ካዝናውን ለመሙላት ብቻ፤ እጅግ ጠባብና የዘቀጠ እኩይ አላማን በመወጠን፤ ሆን ብሎ እመራለሁ የሚለውን ህዝብ ደህንነትና ህልውናን በተደጋጋሚ አሳልፎ እየሰጠ፤ በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሃገራት የሚኖር ህዝባችንን በየአቅጣጫው ለስቃይ በመዳረግ ላይ የሚገኘው፤ የወያኔ/ኢህአዴግ መንግስት ብቻና ብቻ እንደሆነ ንቅናቄአችን በፅኑ ያምናል።

የኢትዮጵያ ወጣቶች ብሄራዊ ንቅናቄ በዚህች ድቅድቅ ጨለማ ቀን ህይወታቸውን ላጡ ወገኖቻችን ቤተሰቦች መጽናናትን አጥብቆ እየተመኘ፤ በኢትዮጵያዊነት ላይ የሚደርሱ እነኝህና ሌሎች መሰል ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶች በህዝባችን ላይ ዳግም እንዳይደርሱ ለመከላከልና ዘለቄታዊ መፍሄ ለማበጀት፤ የችግሩ መንስኤን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከምንጩ ማድረቅ ወሳኝ መሆኑን በፅኑ ያስገነዝባል። ስለሆነም ለዜጎቹ ደህንነትና ለብሄራዊ ህልውናችን ቅንጣት ታህል የማይጨነቀው የወያኔ/ኢህአዴግ ፀረ-ህዝብ አምባገነናዊ መንግስትን በአንድነት በቃህ ማለት የሁሉም ዜጋ ወቅታዊና ታሪካዊ ግዴታ መሆኑን በማስመር፤ ለተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ለሲቪክ ማህበራት፣ ለሁሉም የማህበረሰብ አክቲቪስቶችና የሰብዓዊ መብት ታጋዮች፣ በዋነኝነት ደግሞ ለኢትዮጵያውያን ወጣቶችና ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ፣ ልዩነቶቻችንን ወደ ጎን ትተን ለነፃነታችን በጋራ የምንታገልበት ወሳኝ ወቅት ላይ መሆናችንን እያሳሰበ፤ ሃገር የማዳን ጥሪውን በአክብሮት ያቀርባል።

የኢትዮጵያ ወጣቶች ብሄራዊ ንቅናቄ